<u>የምስጋና መዝሙራት</u>

1. እግዚአብሔር ይመስገን

እግዚአብሔር ይመስገን ይህችን ቀን ቀድሶ ለሰጠን እኽ (2)

ከያለንበት ሰብስቦ (2) ለዚህ ያደረሰን (2)

2. ለጌታዬ ለእግዚአብሔር

ለጌታዬ ለእግዚአብሔር ስላደረገልኝ ምን እከፍለዋለው

ላመስግነው እንጂ/2/ሌላ ምን እላለሁ

3. ለዚህ ላደረሰን

ለዚህ ላደረሰን በሰላም በጤና/2×/

ሃሌ ሃሌ ሉያ(2×) እናቅርብ ምስጋና/2×/

4. አስተምሮናልና

አስተምሮናልና መክሮናልና ገስፆናልና(2)

እግዚአብሔር ይድረሰው ምስጋና(2)

5. ንሴብሐ

ንሴብሐ /2/ ለእግዚአብሔር /2/

ስቡሐ ዘተሰብሐ /4 /

እናመስግነው /2/ እግዚአብሔርን /2/

ምስጉን ነው የተመሰገነ /4/

ባህሩን ተሻግረን ወንዙ ደረቅ ሆነ

በጠላታችን ላይ ድሉ የኛ ሆነ

ከባርነት ቀንበር ፍፁም ነፃ ወጣን

ህይወት የሚሰጠን መና ነው ምግባችን

አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር

ሁሉንም አለፍነው አምላካችን ይክበር

ጉልበታችን ቢዝል መከራም ቢበዛ

ሃይላችን ጌታ ነው የዓለሙ ቤዛ

ከአለት ላይ ውሃ ፈልቆ እንደጠጣነው

ይህን ታላቅ አምላክ ኑ እናመስግነው

ሰዎች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል

ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል

አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር

ሁሉንም አለፍነው አምላካችን ይክበር

ጉልበታችን ቢዝል ፈተናው ቢበዛ

ሃይላችን ጌታ ነው የዓለሙ ቤዛ

6. ደስ ይበለን

ደስ ይበለን/2×/

አምላክ አለ መሃላችን

ምን ይከፈል ለዚህ ስራህ

ገናና ነው አምላክ ክብርህ

ምሕረቱን አይተናልና

አድርሶናል አምላክ በጤና

ይህችን እድሜ ለጨመረልን

ለንስሐ ጊዜ የሰጠን

ኃጢአትህን ይታገስሀል

በምሕረት አምላክ ያይሀል

ደስታ ነው በሰማያት

የአንድ ኃጥእ የጽድቅ ህይወት

እልል በሉ የጎበኛችሁ

በምሕረት አምላክ ያያችሁ

በችግር ቀን ላሰበን ሁሉ

አመስግኑ ዝምም አትበሉ

ድንግል ማርያም ትጸልያለች

ኃጥኡን ሰው ማረው እያለች

በድንግል ክብር እንኖራለን

በጽኑ ፍቅር አምላክ ያስበን

7. ኑ በእግዚአብሔር

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን(2×)

ለታላቁ ክብር ለዚህ ላበቃን

ከሞት ወደ ህይወት ላሸጋገረን

ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንግል ደስ ይበለን/2×/

የሰማዩን መንግስት ርስቱን ለሰጠን

ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሳየን

ለዚህ ድንቅ ውለታ ምስጋና ያንሰዋል

በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል

ከዐለት የፈለቀ ውሃ ጠጥተናል

ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል

ፍቅርህ የበዛ ነው ምን ልክፈልህ ጌታ

ስምህን ላመሰግነው ከጠዋት እስከ ማታ

በቃዴስ በረሃ ምንም በሌለበት

በኤርትራ ባህር ወጀብ በበዛበት

ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምን ተሰኖት

ልባችሁ አይፍራ በፍጹም እመኑት

በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም

ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም

ያጣነውን ሰላም ዛሬ አገኘን

እጅግ ደስ ይበለን በእመቤታችን

የሐና የኢያቄም የእምነታቸው ፍሬ

በእግዚአብሔር ፈቃድ ተወለደች ዛሬ

የኢያቄም ስእለቱ የሐና እምነት

ለምኚልን ለእኛ ኪዳነ ምሕረት

8. አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነትህ

አመሰግንሃለሁ እልል(2×)

ለዓለመ ዓለም አማኑኤል

እገዛልሃለሁ መድኃኔዓለም

ቀኑ ጨልሞብኝ ዙርያው ገደል ሆኖ

የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ

ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ

ፈጽሞ አራቅህልኝ የልቤን ትካዜ

አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ

ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ

እንደማትተወኝ አሁን አውቄያለሁ

ካለኝ ነገር ሁሉ በአንተ ታምኛለሁ

ጥቂቷን አብዝተህ የምትመግብ ጌታ

የምመልስልህ ባለገኝ ስጦታ

በቀንም በሌሊታ ሁሌ የሚያበራ

መንክር ለባህሪህ እጹብ የአንተ ስራ

አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል

ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል

ደህ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና

ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎድል እንደገና

9. አንደበቴም ያውጣ

አንደበቴም ያውጣ የምስጋና ቅኔ

የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ በዓይኔ

በገባዖን ሰማይ ፀሐይን ያቆመ

ዛሬም ጉብኝቶኛል እየደጋገመ

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ

ከኃጢያት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ

የአናብስቱን አፍ በኃይሉ የዘጋ

የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኛጋ

በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ

ከቅዱሳን ጋር ስዘምር አብሬ

እርሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብትስቅብኝ

ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ

አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድም

ለጣኦት እንድሰግድ ነገስታት ቢያውጁም

ሁሉም ቢተወኝም ቢጠላኝም ዓለም

ፅናት ይሆነኛል ጌታ መድሃኔዓለም

10. እንደ እግዚአብሔር ያለ

እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለምና/2×/

እልል በሉ ቁሙ ለምስጋና/2×/

ባህር ተከፈለ እስኪታይ መሬቱ

ፈርዖን ወደቀ አልሰራም ትምክህቱ

ደካሞቹ ጸንተው ተራመዱ

ኃይለኞቹ ይኸው ተዋረዱ

የኢያሪኮ ቅጥር የማይደፈረው

ይኸው ፈራረሰ የሰው እጅ ሳይነካው

ኃይለኞቹ ቢበረታቱብን

እንጸናለን በእርሱ ተደግፈን

የተወረወረው የጠላታችን ጦር

ሜዳ ላይ ወደቀ ጋሻ ሆኖ እግዚአብሔር

የድንግል ልጅ እኛ የምናመልከው

ከሀሊ ነው የለም የሚሳነው

11. ስለማይነገር ስጦታው

ስለ ማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ቸል ያላለን አምላክ ስንጓዝ ማዕበሉን አቋርጠን
ስለ ማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

አዝ
የሕይወት እስትንፋስ ዘራብን ሕያው እንድንሆን
ይህን ያደረገ አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን
ስለ ማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

አዝ
ነፋስን ገስፆ ማዕበል አቁሞ ሚያሻግር
የዓለም ፈተና ቢበዛ እሱ መጠጊያችን
ስለ ማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

አዝ
ዳግም እንዳንሞት በሞቱ ሞትን የረታልን
የምንመካበት ትንሣኤ ሰላምን ለሰጠን
ስለ ማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

አዝ
ከሲኦል እስራት ተፈተን ነጻ የወጣንበት
መስቀሉን ለሰጠን ለአምላካችን እንዘምር በእውነት
ስለ ማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገ

አዝ
ነፋስን ገስፆ ማዕበል አቁሞ ሚያሻግር
የዓለም ፈተና ቢበዛ እሱ መጠጊያችን
ስለ ማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

12. ላመሰግንህ የኔ ጌታ

ላመሰግንህ የኔ ጌታ ላመሰግንህ

ልቀኝልህ የኔ ጌታ ልቀኝልህ

ህይወቴ ነው ዝማሬዬ ትሩፋቴ

የሰጠኸኝ እንዳከብርህ አንተ አባቴ)(2)

ከኔ ሆነህ የምሰጥህ ባይኖረኝም

ከሰጠኸኝ የአንተን መስጠት አይከብደኝም

ጥበቤ ነህ የምስጋና መሰረቴ

ዝማሬዬን ያፈሰስከው በህይወቴ

አንደበቴን የቃኘኸው ለምስጋና

ይኸው ውሰድ ቅኝትህን እንደገና(2)

ባዶ እኮ ነኝ የኔ ጌታ ምን ልቅዳልህ

በእጄ ላይ አንዳች የለኝ የምሰጥህ

ላንተ ክብር የሚመጥን ህይወት የለኝ

ዝማሬዬን በቸርነት ተቀበለኝ

አንደበቴን የቃኘኸው ለምስጋና

ይኸው ውሰድ ቅኝትህን እንደገና(2)

ከምድር ላይ ከአፈር ስትፈጥረኝ

ከምስጋና የተለየ ምን ስራ አለኝ

ቀንና ሌት በመቅደስህ እቆማለሁ

አምላኬሆይ ሳወድስህ እኖራለሁ

አንደበቴን የቃኘኸው ለምስጋና

ይኸው ውሰድ ቅኝትህን እንደገና(2)

እዝራ ስጠኝ የከበረ መሰንቆህን

ዳዊት ስጠኝ የሚፈውስ በገናህን

መዝሙር ቅኔ ተምሪያለሁ ከአባቶቼ

እዘምራለሁ ባንተ ፍቅር ተመርቼ

አንደበቴን የቃኘኸው ለምስጋና

ይኸው ውሰድ ቅኝትህን እንደገና(2)

13. ሰላም ሰላም ለኪ

ሰላም(2) ለኪ ማርያም ሰላም ለኪ(2)

የሕይወት መሠረት..... ሰላም ለኪ

የፍጥረት አለኝታ .....ሰላም ለኪ

ድንግል አደራሽን .....ሰላም ለኪ

ሁኝልን መከታ..... ሰላም ለኪ

በላዔ ሰብ ዳነ .....ሰላም ለኪ

ብዙ ነፍስ አጥፍቶ .....ሰላም ለኪ

ያንቺን ስም ለጠራ .....ሰላም ለኪ

ጥርኝ ውኃ ሰጥቶ .....ሰላም ለኪ

ተማጽነንብሻል .....ሰላም ለኪ

ባማላጅነትሽ..... ሰላም ለኪ

ድንግል አደራሽን .....ሰላም ለኪ

አማልጅን ከልጅሽ..... ሰላም ለኪ

እኛም እንከተል .....ሰላም ለኪ

በጎ ምግባርን .....ሰላም ለኪ

በሰላም በጤና .....ሰላም ለኪ

እንኖራለን .....ሰላም ለኪ

14. ክብረ ቅደሳን

ክብረ ቅደሳን ይእቲ /2/ ክብረ ቅደሳን /2/

ሙዳዬ መና ግሩም /4/ ሙዳዬ መና /2/

የቅደሳኑ ክብር ነሽና

እንሰጥሻለን ቅኔ ምስጋና

የወለድሽልን የህይወት መና

ዝናብ ያለብሽ ታናሽ ደመና

ትህትና ልብስሽ ፍቅር ውበትሽ

ፅንስ ያዘልላል ሠላምታ ድምፅሽ

እሳቱን ወልደሽ እሳት ታቅፈሻል

ሳንዘምርልሽ መቼ ይይመሻል

የፀሐይ መውጫ ምስራቅ ሆነሽ

ታላቁን ብርሀን አየንብሽ

አትጨልምም ህይወታችን

ልጅሽ ስላለ ፀሐያችን

ሰዓሊለነ ሰላም ለኪ

ተማህፀነ በኪዳነኪ

ንዒ ርግብዬ ምስለ ወልድኪ

ሰማይ ወምድር ያወድስኪ

15. የፍቅር እናት

የፍቅር እናት የሰላም /2/

ይናፍቀኛል ስምሽ ሳልጠራው ስቀር ማርያም

በሕይወቴ ውስጥ በኑሮዬ

ቅደሚ ከፊት ከኋላዬ

ተደላደለ ልቤ

አንቺ አለሽና ከአጠገቤ

ምኞቴም ይሰመር ድብቅ ህልሜ

ልለፍ ወጀቡን ተቋቁሜ

የጌታዬ እናት ነሽ

ኃይሌን ያደርጋል ጸሎትሽ

እንዴት እቀራለሁ ከመንገዴ

አደራ እናቴ አስቢኝ

ለሚያስጨንቀኝ ጠላት

ለሚያሳድደኝ አትስጪኝ

ትናንትም ዛሬም አመስጋኝ ነኝ

የለም ለነገ የሚያስፈራኝ

ሜዳ ይሆናል ተራራ

ልጅሽ ስላለ ከእኔጋራ

16. ለማርያም

ለማርያም/2/

እንዘምራለን ለዘለዓለም/2/

የተዘጋች ደጅ - - - - - ለዘለዓለም

ህዝቅኤል ብሏል - - - - - ለዘለዓለም

ንፅሕት ናት በእውነት - - - ለዘለዓለም

በፍጹም ድንግል - - - - - ለዘለዓለም

አብነት አድርገን - - - - - ለዘለዓለም

አኛም እርሱን - - - - - ለዘለዓለም

በፍፁም ፍቅር እንዘምራለን/2/

የዋህይት ርግብ - - - - - ለዘለዓለም

ሰላም አብሳሪ - - - - - ለዘለዓለም

ለጨለማ ሕይወቴ - - - - - ለዘለዓለም

ብርሃንን አብሪ - - - - - ለዘለዓለም

እማጸንሻለሁ - - - - - ለዘለዓለም

ድንግል ለነፍሴ - - - - - ለዘለዓለም

አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ/2/

እጅግ የበዛ ነው - - - - - ለዘለዓለም

ያለኝ ፍቅር - - - - - ለዘለዓለም

አይወሰንም - - - - - ለዘለዓለም

አይነገርም - - - - - ለዘለዓለም

በእርሷ ደስ ይለኛል - - - - - ለዘለዓለም

ሐሴት አደርጋለሁ - - - - - ለዘለዓለም

ስሟን እየጠራሁ እዘምራለሁ/2/

ነይ ነይ ስላት - - - - - ለዘለዓለም

ቀንና ሌሊት - - - - - ለዘለዓለም

አትለየኝም - - - - - ለዘለዓለም

ለእኔስ ቅርቤናት - - - - - ለዘለዓለም

እፁብ እፁብ ብለው - - - - - ለዘለዓለም

አመሰገኗት - - - - - ለዘለዓለም

ክብሯን ሊገልፁት ቢያጥራቸው ቃላት /2/

17. ስምሽን ጠርቼ

ማርያም ብዬ መች እወድቃለሁ
የምጽናናበት ስምሽ ነውና
ድንግል ሆይ ላቅርብ ላንቺ ምስጋና
ጨለማ ውጦኝ በጠላት ሀገር
ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር
ዲያብሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ
የዓለሙን መድኅን ወለድሽልኝ
ከአባቶቼ ርስት ከሀገር ወጥቼ
በአሕዛብ ሀገር ስኖር ተሸጨ
ደርሰሽ አጽናንተሽ አከበርሽኝ
ብቸኝነቴን አስረሳሽኝ
ድንኳኑ ሞልቶ ሰዉ ታድሞ
አስተናባሪው በቄንቀት ቆሞ
ምን አቀርባለው ብዬ ስቸገር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር
ያሰብኩት አሳብ ደመና ሆኖ
ቢበተንብኝ እንደ ጉም ተኖ
ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀርም
በእመአምላክ እኔስ ተስፋ አልቆርጥም
እናት አባቴ ባያስታውሱኝ
ይህቺ ዓለም ንቃ ገፍታ ብተወኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ
ዐውሎ ነፋሱን ባሕሩን አልፋለሁ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ
መከራ አብዝቶ ቢያሰቃየኝ
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና
ክፉዎች ደርሰው ቢዝቱብኝ
አንቺን መውደዴን አያስተውኝ
በአሕዛብ መሐል ስምሽን ስጠራ
መከታ ሁኚኝ እናቴ አደራ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ
መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና

18. ብዙ ልጆች አሉት

ብዙ ልጆች አሉት ለስሙ ምስክር
በዙሪያው ያሉትን አብቅቷል ለክብር
ስለፍፁም ምልጃው ለኔግን ይለያል
መላኩ ሚካኤል ስለው ደስ ይለኛል
ከመላዕክት ክብሩ ከፍ ከፍ ብሎ
በአምላኬ ተሾመ ዘንዶውንም ጥሎ
አሳዳጊዬነው ሆኖ እናት አባቴ
ሚካኤል ባለበት ይሸሻል ጠላቴ
ከሚታየው ሁሉ ልቤ ከሚፈራው
ካላየሁት ነገር ጠላት ከሰወረው
ያድነኛል ፈጥኖ በመንገዴ ወቶ
ሚካኤል ሀያሉ ክንፎቹን ዘርግቶ
በባህራን ታሪክ በነተላፊኖስ
በአፎምያ መትረፍ በነ ዱራታኦስ
በነብዩ ዳንኤል መች ይፈጸምና
የሚካኤል ስራ ይቀጥላል ገና
በጉዞ የረዳቹ በባህር በየብሱ

ፈጥኖ ደርሶላቹ እንባን ስታፈሱ

ስለታችሁ ሰምሯል ቁሙ ለዝማሬ

በሚካኤል ምልጃ የቆማችሁ ዛሬ

ክብር ለሚገባው ክብርን እንሰጣለን

ንጉሥ ለወደደው አንሰግድለታለን

እንኳን ለሚካኤል ለሚቆም ጌታ ፊት

ክብርን እንሰጥ የለ ለምድር ሹማምንት